# “ መለስ ተው ተመለስ ”

የጎጡ ‘ሊቃውንት’ የተጣበበኡት፤
ደደቢት በረሃ አሣር የአማጡት፤
አገር ሊያዋልዱ በእናትዎ እትብት፤
ክህደት ከአባትዎ ወርሰው ጥላሸት፤
‘ጥቁር ደም’ አቃቡን **‘በቀዩዋ’** መሬት፤
አንገት ሰልበው ገቡ አገር በስለት፤
ተጎናጸፉና በኢትዮጵያ እምብርት፤
ልምድ አዋላጅ ሆኑ መንደር መበለት፤
በኩር ልጅ አስክደው ‘ጉዲ-ፈቻ’ አሷት፤
ወራሽ አወራራሽ ሁለት አገር-ቤት፤
አጥር እየሸጡ ለእሳት ጐረቤት፤
ያቀጣጥሉናል መለስ በንዴት፤
**እኰ እንዴት ይማራል ነፍስ ስጋዎት።**

ከእናት አገራችን ‘ጦስ ደቅሎዎት’፤
እምነት ያጎደሉ ልክ እንደ ‘ጉዲት’፤
የሐገር፤ የታሪክ ዘመነ ጥፋት፤
ቆራጭ ፈላጭ ሆነው ምጧን አበዙት፤
ማሕጸኗን አዙረው ማኸን ሊያደርጓት፤
ጽንሷን አቆራርጠው በክለው አንጀት፤
የልጆቿ አበሳ አሳር በዝቶባት፤
ወልዳም ታምልጣለች፤ነፍሰ-ጡሯ እናት፤
**‘የእንግዴ ልጅ’ ሸሏ ጠንቅ ቀብሮባት።**

አልባሳቷን ገፈው ነጠላ አስደፏት፤
ትውልድ አቀባበረው  የነገሱባት፤
የሆዷን ለቃቅመው ጦም አሳደሯት፤
አሳር አቆራኙተው ውራጅ ቅኝ ግዛት፤
ከታሪክ ይማሩ ምህረት በኃዎት፤
ጉልበት ንብረትዎ ስልጣንዎ ፊት፤
ተሸከርካሪው ወንበር ሳያነጥረዎት፤
**መለስ ይመለሱ ቀን ሳያጥረዎት።**

የጎንቻው!  yegonchaw@yahoo.co.uk

*በቅርቡ ለሕትመት ከሚበቃው “የግጥም ስንክሳር መጽሃፉ” የተውሰደ.*

EthioLion.Com